*Yeniser Ayen via Sintayehu Ashine Retta*

# ...............ጦር ፡ ኃይሎች.................

*የዓየሩ ፡ የየብሡ ፡ የምድሩ ፤*
*የነጎድጓድ ፡ የማዕበል ፡ የ ኟመሩ ፤*
*የ ሕቡር ፡ የ አንድነት ፡ ጥማር ፡ ቀመሩ ፤*
*ብረት ፡ ለብሦ ፡ ዘብ ፡ የቆመ ፡ ለ ሃገሩ ፤*
*ሰንደቅ ፡ ዓላማው ፡ የማንነቱ ፡ ማሕተሙ ፤*
*ኢትዮጵያ.....እናት.....ሃገሩ ፤*
*የ አፍሪካ ፡ ቀንድ ፡ ነው ፡ ዳርድንበሩ ፤*
*ቀይ ፡ ባሕር ፡ ነው ፡ የየብስ ፡ በሩ ፤*
*የ ሃገር ፡ አሌንታ ፡ ለወገን ፡ መኪታና ፡ ክብሩ ፤*
*ድንበር ፡ ያስከበረ ፡ የጠበቀ ፡ በ አጥንት ፡ በ ደሙ ፤*
*ወታደርነት ፡ ነው ሕያው ፡ ምስክሩ ፤*
*..እንደ ፡ የብረት ፡ ሠንሰለት ፡ የተሣሰረ ፡ ተጎንጉኖ ፤*
*..በ ዕርዮተ ፡ ዓለም ፡ የተሣለ ፡ ተቀርፆ ፤*
*..በ ምሁራን ፡ መኮንኖች ፡ የ ተገራ ፡ ተገስፆ ፤*
*..በ ሃያላን ፡ ጀግኖች ፡ መሪዎቹ ፡ ተከና ፡*
*..የ አያት ፡ ያባቱን ፡ የ ጀግንነት ፡ ወኔ ፡ ተላብሶ ፤*
*ቃል ፡ ገብቶላት ፡ ለ እናት ፡ ሃገሩ ፡ ለ ኢትዮጵያ*
*.....በ አንድነት ....ቆሞ.......ብረት ፡ ሆኖ.......ብረት .....ለብሶ ፤*
*መለዮዋን ፡ ለብሶ ......ባንዲራዋን .....አቅፎ ፤*
*ኢትዮጵያ ፡ ውይም ፡ ሞት .....ብሎ .....ምሎ ፤*
*በዘር ፡ በ ጎሣ ፡ ሳይሆን ፡ በ ክ/ጦር ፡ ተጣምሮ ፤*
*ተጠራ ፡ ሕብረ ፡ ብሔር ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ተብሎ ፤*

..በ ዓየር ፡ እንደ ፡ ንሥር ፡ አሞራ ፡ በራሪ ፤
..አክናፍ ፡ ክናፍ ፡ ሞገድ ፡ ሰበቃ ፡ ፈጣሪ ፤
..ቆላ ፡ ደጋዉን ፡ ተራራዉን ፡ አናጋሪ ፤
..በ የብስ ፡ በ ባሕሩ ፡ እንደ ፡ ዓሣናባሪ ፤
..ማዕበሉን ፡ ቀዛፊ ፡ ስምጥ ፡ ጠላቂ ፤
..የባሕር ፡ በሩን ጠባቂ ፡
..በ ምድር ፡ እንደ ፡ ቀበሮ ፡ ምሽግ ፡ ፍሮ ፤
..እንደ ፡ ቆቅ ፡ ሆኖ ፡ ጠብቆ ፤
..እንደ ፡ እባብ ፡ ተስቦ ፡ ተመሣስሎ ፤
..ጠላት ፡ ጎራ ፡ ሄዶ ፡ ተፋልሞ ....በ ሣንጃ ፡ ተሞሻልቆ ፤
..የመጣበትን ፡ ጠላት ፡ አስጨንቆ ፡ መግቢያ ፡ አሣጥቶ ፤
...የ ኢትዮጵያ ፡ ሠራዊት .......ነበር .....የ ቀድሞ ፤
በዘር ፡ ሃረግ ፡ ያልነቀዘ ፡ በ ኢትዮጵያዊነት ፡ የ ሠረፀ ፤
ኲሩ ፡ አለኚታ ፡ ሠራዊት ፡ የታመነ ፤
..ለ ሃገሩ ፡ የብረት ፡ አጥር ፡ መከታ ፤
..ለወገኑ ፡ የነበረ ፡ አሌኚታ ፤
..የ ሕይወት ፡ መስዋዕትነት ፡ የከፈለ ፤
..የ አጥንቱ ፡ እንክልካይ ፡ የጋየ ፡ የ ፈመ ፤
..በ ደሙ ፡ ጠብታ ፡ ባንዲራዋን ፡ ያቀለመ ፤
..ማንነቱን ፡ ያለወጠ ፡ ሃገሩን ፡ ያልከዳ ፤
..በ ዕምነቱ ፡ ፅኑ ፡ በ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ያልቸፈተ ፤
..የ ሕዝብ ፡ አካል ፡ ከ ሕዝብ ፡ ያልራቀ ፡.....ያልሸሸ......ያልተጠየፈ ፤
..የነበረዉን.....ያለዉን.......ለ ወገኑ .....ያካፈለ ፤
..ኢትዮጵያዊነቱን .....ያጠበቀ.....ባሕሉን.......የጠበቀ ፤
የ ቀድሞ ፡ ሠራዊት ......በ ኢትዮጵያዊው ......ተናፈቀ ፤

ሊ/ሲ...እንግዳ
0፬/0፩/፲፫

ጦር ኃይሎች